የሰ/መ/ቁ. 34280

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ግርማይ ደስታ - ጠበቃ ረዳኢ ባራኪ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ዓቃቤ ሕግ - ሚሊዮን ተዘራ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19769 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33217 ጥቅምት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል በማለት ዓቃቤ ሕግ ክስ አቅርቦበት፣ ፍርድ ቤቱን የግራ ቀኙን ክስና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 22ን እና ሌሎች ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ፣ አመልካች በአምስት ዓመት እስራት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ፣ ቅጣቱን በሶስት ዓመት ገድቧል፡፡ ዓቃቤ ሕግ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በሌለበት ይግባኙን ከሰማ በኋላ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቅጣቱን መገደቡ ሌሎችን ሊያስተምር የሚችል አይደለም በማለት ከፍተኛው ፍርድ ቤት



የሰጠውን የሶስት ዓመት የገደብ ውሣኔ በመሻር አመልካች አምስት ዓመት እስራቱን እንዲፈጽሙ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፣ ችሎቱ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ የሚያስለውጥ ምክንያት የለም በማለት አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው፣ ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ነው፡፡ አመልካች በጠበቃቸው በኩል ባቀረቡት ማመልከቻ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁን በአግባቡ ሳይገነዘቡና ሣይተረጉሙ በመሆኑ መሠረታዊ ስህተት አለበት በማለት ዝርዝር ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን፣ በዓቃቤ ሕግም በኩል በሰበር ደረጃ ጥፋተኛነቱን ለማስለወጥ ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ አለመሆኑንና የቅጣት ገደቡ መነሣቱ ተገቢ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ በሰበር የሚታረም አይደለም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ከቅጣት ውሣኔ አሰጣጥና ቅጣትን ስለመገደብ ከተቀመጡት የወንጀል ሕግ መርሆች አንፃር ሲታይ ቅጣትን ለማስተማሪያነት ሣይሆን በመበቀያነቱ ለመጠቀም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው የሕግ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው፡-

- በሰበር ደረጃ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?
- በሥር ፍርድ ቤቶች ቅጣቱን ለመገደብና ቅጣቱን ተፈፃሚ መሆን አለበት በማለት የተለያየ ውሣኔ የሰጡበት የቅጣት ውሣኔን

ስለመገደብ የተደነገጉ ድንጋጌዎች በምን አይነት ሁኔታ መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል አለባቸው የሚሉትን ነጥቦች መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ ቅር በመሰኘት በመጀመሪያ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የነበረባቸው ሲሆን ይህንን ማድረጋቸውን የፍርድ ቤቱ መዝገብ አያሣይም፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ይግባኝ ሰምቶ በቅጣት ውሣኔው ላይ የተሰጠውን የሶስት ዓመት ገደብ በመሻሩ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በጥፋተኛነት ውሣኔው ላይ፣ የነበራቸውን ቅሬታ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ በማቅረብ እስከ ሰበር ድረስ በማምጣት መከራከር ነበረባቸው፡፡ አመልካች ይህንን ሥርዓት ተከትለው፣ በጥፋተኝነት ውሳኔው ላይ ተፈጽሟል የሚሉትን የህግ ስህተት ባላቀረቡበት ሁኔታ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔውን መገደቡ ተገቢ አይደለም ብሎ ዐቃቤ ሕግ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት አድርገው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት የሰበር መከራከሪያ ነጥብ ማድረጋቸው የህግ ድጋፍ የሌለውና ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ በመሆኑ፣ አልተቀበልነውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ፣ ፍርድ ቤት በአንድ ሰው ላይ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠ በኂላ የቅጣት ውሳኔውን ለመገደብ እንደሚችልና የቅጣት ውሳኔው ሊገደብላቸው የሚገባው ምን መሰረታዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 192 ላይ መሰረታዊ መርሁ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅጣት የወሰነው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔውን ከመገደብ በህግ የሚከለከልበት ሁኔታ እንዳለና ይኸም የህግ ክልከላ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 የተደነገገ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአምስት ዓመት እስራት ቅጣት በሶስት ዓመት መገደቡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የማይጥስና በሕጉ የቅጣት ውሣኔ እንዳይገደብ የተደነገገውን ክልከላ ተላልፎ፣ የሰጠው አይደለም፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔውን ሲገድብ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 የተደነገገውን የሕግ ክልከላ አልተላለፈም ካልን በሁለተኛ ደረጃ የሚነሣው ጥያቄ አመልካች ቅጣቱ የተገደበለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጡትን መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ በመገኘቱ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣቱን የገደበው አመልካቹ ከዚህ በፊት በወንጀል ያልተቀጣ በመሆኑና ቅጣቱን ተፈፃሚ ከማድረግ ይልቅ ቅጣቱን መገደቡ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የሥር ፍርድ ቤቶች በዚህ መንገድ አይተው ባሣለፉት ቅጣትን የመገደብ ውሣኔ የይግባኝ ቅሬታ ሊቀርብበት የሚችልና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ውሳኔውን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 መርህ አንፃር በመመዘን ሊሽረው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊያፀናው የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ካየነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአምስት ዓመቱ እስራት ቅጣት በሶስት ዓመት እንዲገደብ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መመርመሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሣኔው በሶስት ዓመት ተገድቦ እንዲቆይ የሰጠውን ትዕዛዝ የሻረው፣ አመልካቹ የቅጣት ገደብ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውንና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጠውን መሠረታዊ መርህ የሚያሟላ አይደለም በማለት ሣይሆን በአመልካቹ ላይ የተወሰነው ቅጣት መገደቡ ሌሎች ተመሣሣይ ወንጀል የመሠራት ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ለማስፈራራትና አመልካችን በመቀጣጫነት በማሣየት ትምህርት ለመስጠት የማያስችል ነው በሚል ምክንያት እንደሆነ በውሣኔው ተልጿል፡፡ አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 የተቀመጠውን መርህ የሚያሟላበት